# ዳሽን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የዳሽን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 31ኛ (ሰላሳ አንደኛ) መደበኛ እና 26ኛ (ሀያ ስድስተኛ አስቸኳይ) ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በሚሊኒየም አዳራሽ ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

| | |
|---|---|
| የአክሲዮን ማኀበሩ ስም | ዳሽን ባንክ አ.ማ. |
| የአክሲዮን ማኀበሩ ዓይነት | የባንክ ሥራ ውስጥ የተሰማራ የአክሲዮን ማኀበር |
| የአክሲዮን ማኀበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ | 12,000,000,000.00 |
| የአክሲዮን ማኀበሩ የምዝገባ ቁጥር | 04/2/01821/88 |
| የአክሲዮን ማኀበሩ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ | አዲስ አበባ ፣ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 09፣የቤት ቁጥር አዲስ |

የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፡ -

1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም
2. ምዕላተ ጉባዔውን ማረጋገጥ
3. የስብሰባ አጀንዳውን ማፅደቅ
4. አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የነባር አክሲዮኖችን ግዥና ዝውውሮችን መወሰን
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ
6. የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ
7. የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና ክፍያቸውን መወሰን
8. በዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተወያይቶ መወሰን
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ክፍያና አበል መወሰን
10. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ

የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየምና ማፅደቅ
2. ምዕላተ ጉባዔውን ማረጋገጥ
3. የስብሰባ አጀንዳውን ማፅደቅ
4. የዳሽን ባንክ አ.ማ. የመመስረቻ ፅሁፍን ስለማሻሻል
5. የባንኩን ካፒታል ስለማሳደግ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን
6. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ

ማሳሰቢያ

• በጉባኤው ላይ በግንባር መገኘት የማይችሉ ከሆነ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፊት ለፊት በሚገኘው የዳሽን ባንክ ዋና መስሪያ ቤት 14ኛ ፎቅ የቦርድ ፅ/ቤት በመቅረብ የውክልና ቅፅ በመሙላት ከስብሰባው ከሶስት ቀናት በፊት ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡
• በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ቀርባችሁ ውክልና የምትሰጡም ሆነ በጉባኤው በአካል የምትገኙ ባለአክስዮኖች ማንነታችሁን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ ሕጋዊ ውክልና ይዛችሁ ለምትቀርቡ ተወካዮች የወካያችሁን ማንነት የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡
• በውል አዋዋይ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ የያዘ ተወካይ ዋና ማስረጃውን እና ኮፒውን ይዞ በመቅረብ በስብሰባው ላይ መሳተፍ ይችላል፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ
ዳሽን ባንክ አ.ማ.